# “ፈረንጅ አምላኩ…” ማን ነው? ፩ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ስለ ራሳቸው ሲናገሩ፥ “እኛ ኢትዮጵያውያን ኩሩ ሕዝብ ነን፣ በራሳችን የምንተማመንና የምንመካ፣ በኮሎንያሊዝም ግኘር እንደ ተጠቁ ሕዝቦች ያይደለን፣ በነፃነትቻችን የምንኮራ ነን። ሌላው ግን እንደኛ አይደለም። ፈረንጅ አምላክነት ያጠቃዋል።” ወዘተ… ሲሉ አልፎ-አልፎ ይሰማል። ለመሆኑ ይህ አባባል በእኛ በኢትዮጵያውያን ሓቅነት አለው ወይ ብለን ስንጠይቅ የሚደንቁ ሁኔታዎችን እናገኛለን።

አንዲት እህታችን ከጥቂት ዓመታት በፊት ከአሜሪካውያንና ከቤተሰቧም ጭምር ገንዘብ አሰባስባ እየላከች አንዱን የአዲስ አበባ ሆስፒታል ስትረዳ ቆይታ፣ ለመጐብኘት ወደ ሀገር ሄደች። ግን ያጋጠማትን ሁሉ ተመልሳ ስትነግረን ለራሷም ማመን እየተሳናት ነበር። ‘እናቴን ይዤ ሆስፒታሉን ለማየት ሄድኩ፣ ግን ዘበኛው አላስገባ ብሎ ከበራፍ ላይ ለግማሽ ሰዓት ያህል በፀሓይ ሲያንቃቃን ዋለ። በመጨረሻም ከዚያ የምትሠራ አንዲት ሴትዮ መጥታ፣ “አለ ቀጠሮ እንዲሁ መጐብኘት አይቻለም፣ ግን ተነገ-ወድያ ብትመጡ እኔ ቀጠሮ ይዤላችሁ አስጐበኛችኋለሁ።” ብላን በከንቱ ወደቤታችን ሄድን። ታድያ በተባለው ቀን እናቴን ዳግም አላደክምም ብየ ብቻየን ሄድኩ። ይሁንና ከመጀመሪያው የባሰ ሁኔታ አጋጠመኝ። አሁንም ዘበኛው ከውጭ ገትሮኝ ስጠብቅ፣ አንድ ላንድሮቨር፣ ሾፌሩ አበሻ፣ ግን ሁለት ፈረንጆች የያዘ ወደበሩ ሲጠጋ፣ “ማን ነህ?” “ምን ትፈልጋለህ?” ብሎ እንኳን ሳይጠይቅ፣ ተሯሩጦ በሩን ከፈተና አስገባቸው።

“እኔም ዘበኛው የሚያውቃቸው፣ ወይ ከዚያው የሚሠሩ ይሆናሉ በማለት ዝም ብየ ለረዥምም ጊዜ ከቆየሁ በኋላ፣ ወደ ሆስፒታሉ የሚገባ እግረኛ እንዳጋጣሚ በማግኘቴ፣ ‘እባክህን ለመጐብኘት ቀጠሮ ያለኝ ሰው ነኝ፣ ለወይዘሮ እንትና ንገርልኝ ብየ ላክሁት። የተባሉት ሴትዮም እየሮጡ መጡና፣ ‘ለምን አታስገባትም? በፊት ከገቡት ፈረንጆች ጋር ባንድነት ለማስጐብኘት እየጠበቅናት እኮ ነው ያለነው!’ ብለው አስገቡኝ። በዚህ ሁኔታ በጣም አዝኜ መጣሁ። በሃገራችን ያለው የፈረንጅ አምልኮና የገጽ አድልዎ እጅግ የሚያሳዝን ሆኖ ነው ያገኘሁት።” እያለች አጫወተችን።

ይህ ነገር በሰፊው በሃገራችን ያለ ሁኔታ ነው፣ ወይስ አልፎ-አልፎ ብቻ የሚታይ ነገር? አዲስ በሽታ ነው፣ ወይስ የቆየና ስር የሰደደ ነው? ምን መድሓኒትስ ይገኝለት ይሆን? ይህን አጣርቶ መመርመር ያስፈልጋል።

**ይቀጥላል**…

# “ፈረንጅ አምላኩ…” ማን ነው? ፪ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

በጥንቱ ጊዜ ከዓስር ዓመታት በላይ ከውጭ ሃገር ተምረው ወደ ሃገራቸው የተመሱት ፊተታውራሪ ተክለ ሃዋርያት ተክለ ማርያም በባዮግራፊያቸው እንዲህ የሚል ጽፈው እናገኛለን፤ “አዲስ አበባ የገባሁ ዕለት ያገሬን ልብስ ለብሼ ነበር። በማግሥቱ ዘመዶቼ አስለወጡኝ። የፈረንጅ ልብስ ያስከብርሃል፣ ያማራው ግን ያዋርድሃል እያሉ መከሩኝ።… በማግሥቱም ወደ ግቢ ሄድኩ፣ እንደ አውሮፓውያን ለብሻለሁ፣ ልብሴ ሁሉ ፓሪስ የተሰፋ ዘመናይ ነው። ወደ ግቢ ስገባ እስከውስጠኛው በር ድረስ ከበቅሎ እንዳልወርድ ዘመዶቼ አስጠንቅቀውኛል። (እንደአማራ ለብሼ ቢሆን መመታት አይቀርልኝም ነበር)፣ በገዛ ሃገሬ ለመከበሪያዬ የሰው አገር ልብስ መከታ ስለሆነኝ ልቤ ተቃጠለ።” በገጽ 146-147 ተመልከት።

ይህ ብቻ አይደለም፣ ገና የባሰም አለ። “…አንድ ቀን ጃንሆይ ወደ አራዳ መምጣታቸውን ሰማሁ። ያራዳ ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ሲሠራ ለማየት መጥተው ከትልቅ ዋርካ ሥር በወንበር ተቀመጡ።…የፎቶግራፍ መሣሪያ ይዤለሁ። ጃንሆይን ለማንሳት ፈቃዳቸው እጠይቃለሁ ብዬ ሄድኩ። ዘበኞቹ እንደጠላት አዩኝ። “ይህ ደግሞ ከየት መጣ፣ አረድያ በለው፣ አታስቀርበው” እያሉ መጠጋት እንዳልችል ከለከሉኝ። ይህን ጊዜ አንድ ልጅ እግር ግሪክ፣ በማናቸውም አኳኋኑ ያልሰለጠነ ከዘበኞቹ ጋር እየተጋፋ መጣ። “አረ ወጊድ ሚኒዲርኖ” እያለ፣ እጆቹን በኪሱ ውስጥ እንደሸጎጠ፣ ባርኔጣውን ቅቢብ አድርጎ እያፏጨ፣ እየተንጎራደደ፣ በጃንሆይ ፊት አወራ። ዘበኞቹም ዝም ብለው ያስተውሉታል። ይህ አኳኋን አስደነቀኝ። ዘበኞቹን ልጠይቃቸው አልኩና ቀረብ ስል ጮሁብኝ። “የት ትሄዳለህ፣ እዚያው ሁን” እያሉ በቁጣ ተናገሩ። ታድያ ደፈርኩና ቀረብ ብዬ ጠየቅኋቸው፤ ‘እኔ እናንተን አልፌ ለመሄድ አልፈልግም፣ አንድ ነገር ብቻ ልጠይቃችሁ እወዳለሁ። ይህ ባለጌ መጤ ግሪክ እንደዚህ በድፍረት እያፏጨ፣ እየተንጎራደደ በጃንሆይ ፊት ሲያልፍ፣ ስለምን አላባረራችሁትም? እኔ ግን ገና በሩቅ ስታዩኝ ስለምን ትጮሁብኛላችሁ?’ አልኳቸው። ከዘበኞቹ አንዱ መለሰልኝ። “እሱ ፈረንጅ ነው፣ አንተ ግን እንደኛው ጥቁር ነህ” አለኝ። በገጽ 156 ተመልከት።

ይህ የሚያሳየን የፈረንጅ አምልኮ በሃገራችን የገባው ዛሬ ሳይሆን ለብዙ ዓመታት የቆየና ስርም የሰደደ በሽታ መሆኑን ነው። ስለዚህ በቀላሉ ላይድን ይችላል። በቅድሚያ ግን ‘ሕመሙን የደበቀ መድሓኒቱን ደበቀ’ ነውና፣ በእርግጥ በሽተኛነታችንን ማወቅና ማመን ያስፈልገናል።

**ይቀጥላል…**

# "ፈረንጅ አምላኩ…" ማን ነው? ፫ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

ቀደም ብለን እንዳየነው 'የፈረንጅ አምልኮ' በሽታ በሆስፒታል ዘበኞችና በቤተመንግሥት አጋፋሪዎች ብቻ የተወሰነ ቢሆን ተመልክተን ማዘን፣ 'ባይማሩ ነው' ብለን በይቅርታና ምክር ማለፍ እንጂ በይፋ ጽፎ ማውጣት ባላስፈለገንም ነበር። ይህ በሽታ ግን በሃገራችን ከላይ እስከ ታች ተጋብቶ የተስፋፋ በመሆኑ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ እንዳልሆነ ቀጥሎ እናሳያለን።

እጅግም የሚደንቅ ያገኘነው ነገር በዩኒቨርሲቲ እና በመንግሥት ትብብር የወጣው የደሞዝ ሰነድ በውጭ ሃገር ሰዎችና በኢትዮጵያውያን መካከል ባለው ጉልህ ልዩነት ነው። የማስትሬት ዲግሪ ላላቸው ኢትዮጵያውያን በ3,380 ብር ብቻ ሥራ ሲያስጀምሩ የውጭ ሃገር ሰዎችን ግን (ከህንድ፣ ከኤውሮጳ፣ ከአሜሪካ) በ$1,500 ያስጀምራሉ። ይህም ወደ አምስት ዕጥፍ የሚጠጋ የደሞዝ ልዩነት መኖሩን ያሳያል። የዶክቶር መዓረግ ላላቸው ኢትዮጵውያን ደግሞ በ4,000 ብር ሥራ ሲያስጀምሩ፣ ለውጭ ሃገር ሰው ግን በ$3,000 ማለትም ከሰባት ጊዜ ዕጥፍ ደሞዝ ይሳጣል። ይህ ታድያ የፈረንጅ አምልኮ በሽታ ካልሆነ በቀር ምን ምክንያት ሊኖረው ይችላል?

ማንም ሰው ማውቅ የሚገባው፣ የውጭ ሃገር ሰው ወደ ሃገራችን ሊሠራ የሚመጣው በሃገሩ ሊያገኘው ከሚችል ደሞዝ በጣም የበለጠ በማግኘቱ እንጂ ለጽድቅ አይደለም። (ይህ በሚስዮን ኃይማኖት ያሉትን ሠራተኞች ላያካትት ይችላል።) በኤውሮጳና በአሜሪካ ከ5% - 10% የሥራ አጥነት፣ በህንድ አገር ደግሞ እንደየቦታው ከ20% - 35% ከዚያም በላይ የሥራ አጥነት እንዳለ ይታወቃል። ይህ ታድያ አገራችን በውድ ዋጋ የውጭን ሰዎች እየቀጠረች፣ የራስዋን ልጆች ግን በዝቅተኛ ዋጋ ቀጥራ መያዟ ለምንድነው? ታድያ የገዛ ልጆቿ ቢሸሿትና ውጭ ቢሄዱ ምን ይደንቃል?

እንግዲያውስ ብዙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን አገር ጥለው በመሄድ ከውጭ ሃገር በተለያዩ መስኮች ተሰማርተው ለመገኘታቸው ምክንያቱ ይኸውና ፍጥጥ ብሎ እናየዋለን። ከባዱ የአዕምሮ ዝርፊያ (Brain Drain) ተብሎ ለሚነገርለትና እስከ ዛሬ መፍትሔ ላልተገኘለት ችግር፣ መንግሥት ይህን የተዛባ የደሞዝ ሰነድ ቢያስተካክልና ቢያመቻች በአጭር ጊዜ ብዙ ባለሞያ ኢትዮጵያውያን ወደ ሃገራቸው ተመልሰው እንደሚመጡና እናት ሃገራቸውን እንደሚያገለግሉ፣ ብዙ ህንዶችና ሌሎች የውጭ ሃገር መምህራንና ሐኪሞችም ወደ ሃገራቸው እንደሚሄዱ ጥርጥር የለውም።

**ይቀጥላል…**